# ለለወጣት ሠራተኞች የተከለከሉ ሥራዎች ዝርዝር እንደገና ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 813/2021

# አስመልክቶ የቀረበ አጭር ማብራሪያ

2013ዓ.ም

አዲስአበባ

1. የመመሪያ ማሻሻል አስፈላጊነት

ሀገራችን ከምታራምደው ምቹ የኢንቨስትመንት አማራጭና ዘርፈ ብዙ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ለበርካታ ዜጎች ጊዜያዊና እና ቋሚ የስራ ዕድሎችን በመፍጠር ላይ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ ዜጎች መካከል ወጣቱ ትውልድ ሰፊውን የሥራ ድርሻ የሚይይዝና ለሀገሪቱ ፈጣን ልማትና የኢኮኖሚ እድገት የላቀ አስተዋጽዖ የሚያበረክት ወሳኝ የህብረተሰብ ክፍል ነው፡፡

በሃገር አቀፍ ደረጃ የኢንዱስትሪ ሰላም እንዲሰፍን፣ በተለይ የወጣቱ የሰራተኛ ደህንነት እና ጤንነት እንዲጠበቅ እና የስራ አካባቢዎች እንዲሻሻሉ ማድረግ ተገቢ በመሆኑ ወጣቱ ትውልድ በስራው ዓለም ላይ ያለውን ሀላፊነት በሚገባ ለመወጣትይችል ዘንድ የስራ ላይ ደህንነቱና ጤንነቱ ለማረጋገጥ የሚያስችል የተሟላ የህግ ማዕቀፍ ማውጣት በማስፈለጉ ከሀገራዊ ህጎች፣ ከኢኮኖሚ እና ከማህበራዊ ፖሊሲዎች ብሎም ከዓለም አቀፍ ስምምነቶች ጋር በማጣጣም መመሪያውን ማሻሻል አስፈልጓል፡፡

2. <u>የመመሪያው ማሻሻያ ዝግጅት ሂደት</u>

በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጀ ረቂቅ መመሪያ ማሻሻያ የበለጠ እንዲዳብርና ሁሉን አቀፍ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ሠ.ማ.ጉ ቢሮ/ኤጀንሲ ፤ ከኢትዮጲያ አሰሪዎች ኮንፌዴሬሽን ፣ ከኢትዮጵያ ሰራተኛ ማህበራት ኮንፌደሬሽን፣ከጠቅላይ አቃቤ ህግና ከሚመለከታቸው ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የውይይት መድረክ በማዘጋጀት ግብዓቶችን በማሰባሰብ ረቂቅ መመሪያውን የመጨረሻ መልክ የማስያዝ ስራ ተሰርቷል፡፡

3. <u>የመመሪያ ዝርዝር ድንጋጌዎች</u>

ለወጣት ሠራተኞች የተከለከሉ ሥራዎች ዝርዝር እንደገና ለመወሰን የተዘጋጀው መመሪያ አስራ ሶስት /13/ **አንቀፆች** አሉት፡፡ የመጀመሪያዎቹ ከ1-4 ያሉ አንቀፆች አጠቃላይ ዋና ዋና ጉዳዮችን የያዙ ሲሆን እነዚህም *አውጪው ባለስልጣን፣ አጭር ርዕስ፣ ትርጓሜና የተፈፃሚነት ወሰን* በሚል ርዕሰ ተከፋፍለው ተቀምጠዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ በአንቀፅ 4 "ትርጓሜ" በሚለው ርዕሰ ሥር መመሪያውን በቀላሉ ለመረዳት ያስችላሉ ተብለው የሚታሰቡ ቃላይ /ሀረጎች ፍቺ ተቀምጧል፡፡

**በአንቀፅ** 5 ላይ ወጣት ሠራተኞች እንዳይሰማሩባቸው የተከለከሉ የሥራ ዘርፎችን

በዝርዝር አስቀምጧል፡፡ይህ አንቀጽ ለመመሪያ መሻሻል ዋነኛ ምክንያት የሆኑ ጉዳዮችን አካቷል፡፡ በመሆኑም የወጣት ሠራተኞችን የሥራ ላይ ደህንነትና ጤንነት የሚያስተጓጉሉ እና ለሥራ ላይ አደጋ እና የሙያ በሽታ የሚያጋልጡ ሥራዎች እና የስራ ዘርፎች ተካተውበታል፡፡ እነዚህ የሥራ ዘርፎች **በአንቀፅ 5 ከንዑስ አንቀፅ (1-14) በዝርዝር** የተቀመጡ ሲሆን ከሌሎች ሠራተኞች በተለየ መልኩ ለወጣቶች እንዲከለከሉ የተደረገበት ቁልፍ ምክንያት የወጣቶች በአካላዊ፣ በእዕምሯዊ ወይም በስነ ልቦና አወቃቀራቸው ገና በማደግ ላይ የሚገኙ በመሆናቸው በተጠቀሱት የሥራ ዘርፎች ላይ ቢሰማሩ ሊደርስባቸው የሚችለውን ከፍተኛ የስራ ላይ አደጋ እና የጤና ችግር ታሳቢ በማድረግ እንዳይሰማሩ ክልከላ ተደርጓል ፡፡

በአንቀፅ 5 ከንዑስ አንቀፅ 1 -2 ክልከላ የተደረጉባቸው የሥራ ዘርፎች (መንገደኞችንና ጭነትን በአየር፣ በየብስና በውሀ የማጓጓዝ ሥራዎች፣ ዓሳ የማስገር፣ በወደቦችና በመጋዘኖች ከባድ ዕቃዎችን በማንሣት፣ በመነተት የሚሰሩ የጉልበት ሥራዎች) በባህሪያቸው ከፍተኛ ጉልበትን የሚጠይቁ የሥነ ልቦና እና የአዕምሮ ጥንካሬን እና በአደጋ ጊዜ የመወሰን አቅም የሚጠይቁ ሥራዎች ሆነው በመገኘታቸው ወጣት ሠራተኞች እንዳይሰማሩባቸው የተከለከሉ ሲሆን፤ እንዲሁም ንኡስ አንቀፅ 3-4 ላይ የተቀመጡት የሥራ ዘርፎች (ከኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ፣ ማስተላለፊያና ከማከፋፈያ ጣቢያዎች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ሥራዎች፣ ከመሬት በታች በሚካሄዱ የማዕድን ቁፋሮ፣ የድንጋይ ካባዎች እና የመሳሰሉ ሥራዎች) በባህርያቸው አደገኛ በመሆናቸውና በወጣቶች ስነ ልቦና ላይ ጫና የሚያደርሱ፣ ከፍተኛ ጥንቃቄንና ጉልበትን የሚፈልጉ፣ በአደጋ ጊዜም የመወሰን አቅም የሚጠይቁ የሥራ ሁኔታ ስላላቸው ወጣቶች እንዳይሰማሩባቸው ተከልክለዋል፡፡

በንዑስ አንቀፅ 6 ላይ የአልኮል፣ የሲጋራ እና ሌሎች ሱስ ሊያስይዙ ወይም ሊመርዙ የሚችሉ ንጥረ ነገሮች ማምረቻ ፋብሪካዎች ላይ መስራትን እንደማይቻል አስቀምጧል፡፡ እነዚህ ሥራዎች በዋናነት የወጣቶችን አዕምሯዊ እና ስነ ልቦናዊ ባህርያት የሚጎዱና ወጣቶቹ በቀላሉ ለሱስ የሚያጋልጡ እና በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሰውነታቸውን ሊመርዙ ሚችሉ የስራ ሁኔታዎች በመሆናቸው ነው፡፡

በንዑስ አንቀፅ 7 እና 8 ላይ ወጣት ሠራተኞች እንዳይሰማሩባቸው የተከለከሉ ስራዎች የሞቃትና የቀዝቃዛ የስራ ክፍሎች ናቸው፡፡ እነዚህ የሥራ ዘርፎች የተከለከለበት ዋነኛ ምክንያት የወጣቶቹ የሜታቦሊዝም (አጠቃላይ የሰውነት ውስጥ እንቅስቃሴን) በከፍተኛ ሂደት ውስጥ እንደመገኘቱ መጠን ከፍተኛ ሙቀትና ቅዝቃዜ

ከበዛባቸው የሥራ አካባቢዎች ላይ የመሳብ ወይም የመጠቃት ሥነ ህይወታዊ ባህሪያቸው ከፍተኛ በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም ወጣት ሰራተኞች በሙቀት እና በቅዝቃዜ ጫና መጎዳትና ለጤና መታወክ ምክንያት ናቸው፡፡

በንዑስ አንቀጽ 9 ላይ የተቀመጡት ጎጂ ለሆኑ የአዮናይዚንግና አዮናይዚንግ ያልሆኑ (የኤክስ ሬይ፣ አልትራቫዮሌት ሬይ፣ ጋማ ሬይ ወዘተ…) ጨረሮች የሚያጋልጡ ሥራዎችን መስራት የወጣቶቹን ተፈጥሯዊ አካላቸው የተጠቀሱትን ጨረሮች በቀላሉ የመሳብ ባህርያት ስላላቸው ነው፡፡

በንዑስ አንቀፅ 10 አደገኛና መርዘኛ የሆኑ ኬሚካሎችን ማለትም አርሴኒክ፣ ሊድ፣ ሜሪኩሪ፣ ካድሚየም፣ ማንጋኒዝ፣ ሳያናይድና የመሳሰሉ ብረታማ ንጥረ ነገሮችና አሚማዎች ሥራ ላይ በሚውሉበት የሥራ ዘርፍ ላይ ወጣት ሰራተኞችን ማሰራት የተከለከለ መሆኑ ተደንግጓል፡፡ እነዚህ የተዘረዘሩት ንጥረ ነገሮች ካርሲኖጀኒክ፣ ኢንዶክርን፣ ኒውሮቶክሲን አመንጪ በመሆናቸው ወጣት ሰራተኞች በከፍተኛ የመገንባት ሂደት ውስጥ (አጠቃላይ የሰውነት ውስጥ እንቅስቃሴ) ከፍተኛ በመሆኑ እና ወጣቶቹም እነዚህን ንጥረ ነገሮች በቀላሉና በከፍተኛ ፍጥነት ወደ ሰውነታቸው ውስጥ የመሳብ ሃይል ስላላቸው ወጣቶቹ ለካንሰር፣ ኢንዶክሪን እና ለነርቭ ህዋሳት ህመም ስለሚጋለጡ ነው፡፡

በንዑስ አንቀፅ 11 ላይ የተቀመጡት የተቀጣጣይነት እና የፈንጂነት ባህርይ ያላቸውን ውህዶች እና ንጥረ ነገሮች በሚመረቱባቸውና አገልግሎት ላይ በሚውሉባቸው ሥራዎች ውስጥ ወጣቶችን ማሰራት የተከለከለ መሆኑ ተደንግጓል፡፡እነዚህ የሥራ ሁኔታዎች በወጣቶቹ ላይ የጤና መታወክ ከማስከተላቸው ባሻገር አጣዳፊ እና ህይወት ቀሳፊ የሆነ ፋታ የማይሰጥ አደጋ የማስከተል ባህርይ አሏቸው፡፡ በዚህ ረገድ የወጣቶቹ የማስተዋልና የማመዛዘን እንዲሁም ጫናዎችን የመቋቋም እና አደጋዎችን በቀላሉ ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥነ ልቦና እና አቅማቸው ዝቅተኛ በመሆኑ በእነዚህ ስራዎች ላይ መሰማራታቸው ለአደጋ ተጋላጭ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

በንዑስ አንቀፅ 12 ላይ የተቀመጡትን ሥራ ሁኔታዎች የተለያዩ የፀረ ተባይ እና የፀረ አረም ኬሚካሎች የማዘጋጀት፣ የመበጥበጥና የመርጨት፣ሥራዎችን

ያካትታል፡፡ እነዚህ የሥራ ሁኔታዎች ውስጥ ያሉ ኬሚካሎች በአመዛኙ ፈሳሽ መሆናቸውና አደጋ የሚያደርሱበት መንገድ በአብዛኛው የመተንፈሻ አካላትን የሚጎዱ እና በንዑስ አንቀፅ 10 ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ናቸው፡፡

ንዑስ አንቀፅ 13 ላይ የተቀመጡት ተላላፊ በሽታዎችን የሚያስከትሉ ስነ ህይወታዊ ጠንቆች ማለትም ከፈንገስ፣ ከባክቴሪያና ቫይረስ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ሥራዎች ላይ መስራትን ይከለክላል፡፡እነዚህ ተህዋሲያን በተለይ የወጣቶቹን በሽታ የመከላከል አቅምን በማዳከም ለተለያዩ የጤና እክሎችን የሚያስከትሉ በመሆናቸው ነው፡፡

በመጨረሻም በንዑስ አንቀፅ 14 ላይ ወጣቶችን አካላዊ፣ አዕምሯዊ እና ስነ ልቦናዊ ጉዳቶች ሊያደርሱ የሚችሉ ስራዎች ላይ ወጣቶችን ማሰማራት ጎጂ እንደሆነ ያስቀምጣል፡፡ይህ ማለት ከሞላ ጎደል አጠቃላይ የወጣቶችን ተፍጥሯዊ ሁኔታ የሚፈታተኑ እና በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የጤና ጉዳት የሚያደርሱ ነገር ግን ከተከለከሉ ሥራዎች ዝርዝር ውስጥ ያልተጠቀሱ ሥራዎችን ያጠቃልላል፡፡

በመመሪያው በአንቀፅ 6 ሌላኛው ትኩረት የተሰጠው ከዕቃዎች ክብደት ጋር የተገናኘ የሥራ ሁኔታ ነው ፡፡ ይህም ወጣት ሰራተኞች በረዥም ጊዜ በሚሰማሩበት የስራ ዘርፍ አልያም በድንገተኛና የአጭር ጊዜ ስራዎች ላይ ጉልበትን በመጠቀም የሚካሄድ ማናቸውም ክብደትን ከቦታ ቦታ የማንቀሳቀስ፣ የመሸከም፣ የማንጓዝ፣ የማንሳት፣ የማውረድ፣ የማውጣት፣ የመጎተት፣ የመሳብና የመሳሰሉትሥራዎችን ያጠቃልላል፡፡ በዚህም የሥራ ሁኔታ ውስጥ ዕቃው (ክብደቱ) የሚንቀሳቀስበት ሁኔታ ማለትም (እንቅስቃሴው ሙሉ በሙሉ በእጅ ሲሆን)፣ የዕቃው ክብደት (ዕቃውን ለማንቀሳቀስ ተከታታይነት ያለው ወይም የለሌው ሥራ) ፣ዕቃው ሚንቀሳቀስበት ሁኔታ (ዳገት የመውጣትና የመውረድ ሁኔታያለበት) እንዲሁም በጋሪ ሆኖ ወለሉ በተስተካከለ ወይም ባልተስተካከለበት የሚል የሥራ ሁኔታዎች በመከፋፈል የወጣት ሠራተኞችን አካላዊ አወቃቀር እና ጉልበት ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ የተፈቀዱ የክብደት መጠኖች ተቀምጠዋል፡፡ የሥራ ቦታዎች በተሽከራካሪ የታገዙም ይሁን ያልታገዙ ሥራው በሚከናወንበት ወቅት በቀጥታም ይሁን

በተዘዋዋሪ ክብደትን የመቀነስ ወይም የመጨመር ባህርይ ሳላላቸውና በወጣቶች ጉልበት ወይም አካል ላይ አላስፈላጊ ጫናን በመፍጠር ጉዳት የሚያደርሱ በመሆናቸው ወጣቶችን ለማሰራት የተፈቀዱ የክብደት መጠኖች እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡

የመመሪያው አንቀጽ 7 ወጣት ሠራተኞች እንዳይሰማሩባቸው የተከለከሉ የሥራ ዘርፎች ተፈፃሚ የማይሆንባቸው ማለትም ኃላፊነት የተሠጠው ባለሥልጣን ባፀደቀውና በሚቆጣጠረው የትምህርትና የሙያ ማሠልጠኛ ተቋማት በሚሰለጥኑና ልምምድ በሚያደርጉ ወጣቶች ላይ መመሪያው ተፈፃሚ እንደማይሆን ይጠቅሳል፡፡ ምክንያቱም እነዚህ የልምምድ ወይም የሥልጠና ተግባራት የሥራ ሁኔታቸው በአሰልጣኞች ወይም በሌሎች ሰዎች እረዳትነት የሚከናወኑ እና ተግባራቱ ተከታታይነት የሌላቸው በመሆናቸው ነው፡፡ በተጨማሪም ረጅም የሥራ ጊዜን የማይወስዱ እና ጉዳት የማድረስ እድላቸውም እጅግ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡

የመመሪያው አንቀጽ 8 ስለ ኃላፊነት የሚያብራራ ሲሆን በዚህም አሰሪ መመሪያውን ከማስፈፀም ረገድ ያለበትን ሀላፊ ያስቀምጧል ፡፡ በተጨማሪም አሰሪው የመመሪያውን ተፈፃሚ ከማድረግ አንፃር ለሚኒስቴሩ/አግባብ ላለው ባለስልጣን በየግማሽ ዓመት አፈፃፀም ሪፖርት ማቅረብ ሀላፊነት ያለበት መሆኑ ተደንግጓል፡፡

በመጨረሻም ከአንቀፅ 9–13 አጠቃላይ ድንጋጌዎ የተቀመጡ ሲሆን እነዚህም ለመመሪያው ተፈፃሚነት የመተባበር ግዴታ፣ ስለ ቅጣት ፣ መመሪያው ስለሚሻሻልበት ሁኔታ እና የቀድሞ በ2005 ዓ.ም ወጥቶ የነበረው መመሪያ የተሻረ መሆኑን የሚገልፁ ናቸው፡፡